የሰ/መ/ቁ. 44545

መጋቢት 07 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ኂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- ክፍሉ መሓሪ - ወኪል ተ/ገብራይ መሓሪ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- በላይ ከመላ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- አቶ ቁሬንሳ ፈይሳ የግል ቤትና ይዞታቸው የሆነውን ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ደስታ ኩምሳ ጋር በመሆን ሐምሌ 21 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ ውል ለአመልካች አባት ለአቶ መሓሪ ገ/እየሱስ ሸጠውላቸው ቤቱን ያስረከቧቸው ሲሆን፤ በእጃቸው ያለውን ቤት በስማቸው እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አድርጐ ባለመቅረቡ የአቤቱታ አቅራቢውን ማስረጃ አጣርቶ ቤቱ በስማቸው እንዲዛወር ሰኔ 08 ቀን 1985 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በኂላ የአሁኑ ተጠሪ ውሳኔውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት በመቃወም አቤቱታቸው ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤትም አቤቱታውን ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) መሰረት በመሰረዝ ገዥ ሻጭን የመጠየቅ መብት አለው በማለት ወስኗል፡፡፡ ከዚህም በኂላ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት የሚገኘው ከወልመራ ወረዳ ግዛት ክልል ወጪ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄን ከመጀመሪያውኑም ቢሆን ተቀብሎ ማስተናገዱ ያለስልጣኑ በመሆኑ ስህተት ነው የሚለውን ምክንያት በመያዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ከዚያም የአሁኑ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኂላ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ይኸው ፍርድ ቤት በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሰጠቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፀናውን ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ነበረው በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ሦስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት የወረዳው ፍርድ ቤት ስልጣን አለው ብሎ የዞኑ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ከሻረ በኂላ ጉዳዩ ወደ ዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተመልሶ እንዲታይ ሳያደርግ መቅረቱ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመረመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጐአል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ታሕሣሥ 06 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ የተፋጠነ ፍትሕ ከማግኘት መብት አኳያ ተገቢ ነው በማለት ውሳኔ ሊጸና ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መሰረት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ይግባኝ የቀረበለት የምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የተመለከተው ከሥልጣኑ ውጪ ነው በማለት ፍሬ ጉዳዩን ሳይመረምር ውሳኔውን መሻሩን፣የክልሉ ሰበር በበኩሉ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው በሚል ምክንያት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሲሽር በፍሬ ጉዳዩ ላይ የዞኑ ፍርድ ቤት እንደገና አከራክሮ እንዲወስን ሳያደርግ መቅረቱን፣ይኸው ፍርድ ቤት ዋናውን ጉዳይ ራሱ የመረመረ ስለመሆኑ በግልጽ ሳያስቀምጥ የወረዳው ፍርድ ቤት የወረዳው የፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የማጽናት ውጤት ያለው ውሳኔ መስጠቱን ነው፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የወረዳው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ የተቀበለበትን ምክንያት አለመግለፁ ወይም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት አለማድረጉ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የራሱን ውሳኔ ካላሳለፈና የበላይ ችሎቱ የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ካልተቀበለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341፣342፣343 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ተገቢውን መወሰን አለበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣንን መሰረት አድርጐ የሰጠውን ውሣኔ ከሻረ በኂላ የወረዳው ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ያለምክንያት ማጽናቱ የአመልካችን የይግባኝ መብት ያጣበበ እና ስነ-ስርአታዊ ያልሆነ ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 49541 ታህሣሥ 27 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሸሯል፡፡
2. በዋናው ጉዳይ ላይ የምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደገና በማየት ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልሰንልታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ